የእግዚአብሔር ቃል

መጽሐፍ ቅዱሳን በልጅነታችን ብዙዎቻችን አንድን ታሪክ በአንድ ጊዜ በማጥናትና ታሪኩን በቀጥታ ከግል ሕይወታችን ጋር በማዛመድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን የምታነቡት እንዴት ነው?

1 የሕግ መጽሐፍ:- ምን ማድረግ እንዳለብኝ ይነግረኛል፣ማድረግ የለለብኝን ያሰጠነቅቀኛል።

2 መንፈሳዊ ጥበቃ:- በየዕለቱ አንድ ቃሉን ዲያብሎስን ያርቃል

3 አቅጣጫ ጠቋሚ (የመሰታወት ኳስ) :- እግዚአብሔር ለወደፊት ሕይወቴ ያለውን ዕቅድ ፣ሰለ ትዳር ጓደኛ፣ ሰለ ሥራ፣ ወዘተ እንዳውቅ ይረዳኛል።

4 መንፈሳዊ ቡና :- እንድነቃ ይረዳኛል ፣ቀኑንም በመልካም ያሰጀምረኛል።

5 የቤተሰብ ሐክም:- መልካም ሰሜት እንድሰማኝ ሰፈልግ ወደ መጽሐፉ እሠራለሁ።

6 ወደ ሑበት የሚያደርሰ ካርታ:- እግዚአብሔር በጤናና በሑበት እንደሚባርከኝ የተሰፋ ቃሉን ይገልጥልኛል።

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ሁሉ መጥፎ አመለካከቶች አይደሉም፣ ነገር ግን የዚህ አመለካከት ዉጤቱ ብዙዎቻችን መጽሐፍ ቅዱስን የጋራ መሪ ሐሳብና ዓላማ የሌለው የተነጣጠሉ መንፈሳዊ ታሪኮች ሰብሰብ እንደሆነ አድርገን እንድናየው ማድረጉ ነው። እውነታው ግን መጽሐፍ ቅዱስ ሰለ እኛ ከመናገር ይልቅ በአብዛኛው ሰለ እግዚአብሔር እርሱ በሕዝቦች መካከል ለመመለክ ሰላለው ናፍቆት የሚናገር ነው።

እግዚአብሔር በምድር ላይ ባሉ ሕዝቦች ሁሉ እንዲከብር ያለውን ናፍቆት የሚናገሩ ከ1600 የሚበልጡ ጥቅሶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ።

ታላቁ ተልዕኮ

እንደ ክርስቲያን እግዚአብሔር ዓለምን እንደሚያይ ማየታችን በጣም አስፈላጊ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለዓለም ካለው ልብ አንጻር ሰንመለከት ከዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ራዕይ ድረስ፣ እናንተን፣ እኔንና የእርሱ የሆነውን ሕዝብ ሁሉ ከራሱ ጋር ሆነን የቀረበውን እያንዳንዱን ሕዝብ ሁሉ ወደ ዙፋኑ እንድናመጣ ሲጣራ እናግኛለን።

ታላቁ ተልዕኮ

ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አንዱ ነው።

ታላቁ ተልዕኮ ታላቅ የተባለበት ምክንያት

1 ሰውን ሁሉ:-

የጌታን ሰም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና ሮሜ 10:13



ብቡ ቁጥር ያላቸው ሕዝቦች ከዓለም አቀፍ ክፍል ጌታን አልተቀበሉም።

“እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?”

— ሮሜ 10፥14

5ቱ እንዴቶች

- ያላመኑበትን እንዴት ይጠሩታል?
- ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ?
- ያለሰባኪ እንዴት ይሰሙታል?
- ካልተላኩስ እንዴት ይሰብካሉ?

- መልካሙን የምሰራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው።

2 ሕዝቡን ሁሉ ስለሚደርስ

“እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

— ማቴዎስ 28፥19-20

አህዛብ:- ሕዝብ ሁሉ ማለት ነው። ራዕይ 5:9-10 7:9-10

በአከባቢያችን የወንጌል ስርጭት የማይሰራው ለምንድን ነው?

- ብዙ የመረዳት ጉድለት ስላሌ
- የተመረጡስዎችኃላፊነት ብቻ ስለሚመስላቸው (የወንገላዊ፣የመጋቢ፣የመድረክ አገልጋይ ብቻ) ስለሚመስላቸው።
- ዋጋ መክፈልን ስለሚፈሩ

3 ፍጥረትን ሁሉ

“እንዲህም አላቸው፦ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ። ማርቆስ 16፥15

ጥሪያችን ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ለመሰበክ ነው።

4 ምዕመናንን ሁሉ

የመሪዎች ኃላፊነት ምዕመናንን ሁሉ ለአገልግሎት ማዘጋጀት ነው። ኤፌሶን 4:11

የምዕመናን ኃላፊነት (1ጴጥ 2:9-10)

- የንጉሥ ካህን ቅዱስ ሕዝብ
- ለርስቱ የተለየ ወገን ከጨለማ ወደ ሚደንቅ ብርሃን የጠራችሁ....

5 ቃሉን ሁሉ መሰበክ

መጽሐፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው። ሉቃስ 24:45

6 የሚኖር ፍሬ

ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ አላችሁና፣ ልትሄዱና ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ ። ዮሐ 15:16

ለታላቁ ተልዕኮ ዋና ዓላማ

እግዚአብሔር በፈጠረው ፍጥረት ሁሉ መታወቅ እና መመለክ የሚፈልግ አምላክ ነው። ለሰውም ልጅ የተልዕኮ ባለአደራነት የተሰጠው እግዚአብሔርን ለዓለም ህዝብ ሁሉ ለማስተዋወቅ ነው። ታላቁ ተልዕኮ እንደ ቃሉም ታላቅ እንደተባለው በሰዎች ሁሉም ልብ ውስጥ ታላቅ ሸክም እና መታዘዝ ኖሮ የሚያመልኩትን አምላክ የሰማይ እና የምድር ጌታን እግዚአብሔርን ለሌሎች እግዚአብሔርን ላላወቁት ሕዝቦች ማሳየት ወይም እግዚአብሔርን በማንነቱ እንዲያውቁ መሰበክ ነው።

ከታታላቆች አባቶች ታሪክ መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና የምናገኘው ቁልፍ ነገር፣ እግዚአብሔር በተለያየ ጊዜ ሰዎችን ቀብቶ ሲያሰነሣ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንድሰራ ሰዎችን ሲያነሣሣ:-

- ሰሙን ለማሰታወቅ፣
- በአህዛብ ዘንድ ሰሙን ከፍ ከፍ ለማድረግ፣
- ከጣዖታት ራሳቸውን ለይተው እርሱን ብቻ እንዲያመልኩ፣
- ሰው የሆነ ፍጥረት ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ፊት መጥተው ነውር የለለበትን መሥዋዕት እያቀረበ እግዚአብሔርን ደስ እንዲያሰኝ ይፈልጋል።

ወደ ውጪ ሄዴን ለሰዎች የወንጌል ሰርጭት ሰናደርግ

ሰዎችን በወንጌል ለመድረስ ውጪ መጥተን የሰርጭት አገልግሎት በምናደርግበት ጊዜ የሚናደርገው ነገር:-

1 ለዳግም ልዴት ጥሪ ማድረግ:- በዚህ ጊዜ ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአተኛ ሰለመሆኑ፣ ከአዳም በተወረሰው ኃጢአት ሙት እንደሆነ ፣ ከዚህ ፍርድ ኢየሱስ ነጻ ሊያወጣ እና ጸጋን ሊሰጥ መሞቱ መነገር አለበት።

- ሰዎች በባህሪያቸው ከእግዚአብሔር የተለዩ መሆናቸው።
- ጽድቅ የሌላቸው እና ከእግዚአብሔር የራቁ ነገር ግን የእግዚአብሔር ክብር የሸፈናቸው መሆኑን።
- ከዚህ ሕይወት ወጥተው ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ የሚችሉት በኢየሱስ ሲያምኑት መሆኑን።
-

2 የንስሐ ጥሪ

እግዚአብሔር ቅዱስ አምላክ ነው። በባህሪውም ቅዱስ የሆነ ነገር የሚወድ ፣ነውር እና እርኩሰት ባለበት ነገር ደስ የማይል አምላክ እንደሆነ፣ ከእርሱም ጋር ቅድስና የለለበትን ነገር የሚያደርጉት፣ክፋ አድራጊዎች፣ ሰሰኞች፣ እና ትዕቢተኞች ሊኖሩ ህብረትም ሊያደርጉ እንደማይችሉ የሚናገረውን የመጽሐፍ ቅዱስን ሐሳብ ማወቅ። ስለዚህ ኃጢአትን የሚያደርጉ ከመንገዳቸው ተመልሰው እግዚአብሔርን ቢፈልጉ የሚምር እና ይቅር የሚል አምላክ እንደሆነ መናገር ነው።